የማይክሮ ፋይናንስ
ተቋም ስም

# የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ስም

# የኤም-ብር አካውንት - የደንበኛ ውልና ሁኔታዎች

## ውልና ሁኔታዎች

ይህ ሰነድ እርስዎ በ አብቁተ አ.ማ. የኤም-ብር የሞባይል ብር ዝውውር አገልግሎት ለሚኖርዎት ተሳትፎ ተግባራዊ የሚሆኑ ሙሉ ውልና ሁኔታዎችን የያዘ ነው፡፡ ከዚህ ጋር አባሪ ሆኖ የቀረበውን የምዝገባ ቅጽ በመፈረም የኤም-ብር አገልግሎት ደንበኛ ሆነው ሲመዘገቡ በነዚህ የአጠቃቀም ሁኔታዎች ለመገዛት ይስማማሉ፡፡ ስለዚህ እርስዎ እነዚህን የአጠቃቀም ሁኔታዎች ማንብብና በሚገባ መረዳት ይኖርብዎታል፤ ካልተስማሙ ለኤም-ብር አገልግሎት ምዝገባውን መቀጠል እና ወይም መጠቀም የለብዎትም፡፡

## ትርጉሞች

**"አካውንት"** ማለት የእርስዎ የኤም-ብር አካውንት ፤በኛ ዘንድ ተመዝግቦ ያለ የኢ-ገንዘብ በየጊዜው በእርስዎ የተያዘ ገንዘብ እና እኩል መጠን ባለዉ በጥሬ ገንዘብ የሚሰላ ነው፤

**"ወኪል"**ማለት በ አብቁተ አ.ማ. የኤም-ብር አገልግሎት ለመስጠት የተወከለ ሰው ነው፡፡ ተጨማሪ ዝርዝር ከ አብቁተ አ.ማ. ይገኛሉ፡፡

**"ጥሬ ገንዘብ "** የፌዴራላዊ ዲሞክሪያሲያዊ ኢትዮጲያ ህጋዊ መገባበያ ገንዘብ ማለት ነው፤

**"ደድማ"** የኤም-ብር አገልግሎት የደንበኞች ድጋፍ ማዕከል በ አብቁተ አ.ማ. የቀረበ ለወኪሎች እና ለየማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ቅርንጫፎች ድጋፍ የሚሠት ማዕከል ማለት ነው፤

**"ኮርፖሬት አካውንት"**; ማለት የኤም ብር አካውንትዎ ሲሆን ነገር ግን ማንኛውንም አየነት የገንዘብ ዝውውር ፤ ወጪ ፤ ገቢ በሞባይል ስልክዎ ማያንቀሳቅሱት ማልት ነው፤.

**"ኢ-ገንዘብ"**; ማለት በእርስዎ የኤም-ብር አካውንት የሚታይ ኤሌክትሮኒክ የገንዘብ መጠን ሲሆን እኩል መጠን ባለዉ በጥሬ ገንዘብ የሚሰላ ሆኖ በኤም-ብር ወኪል ወይም አብቁተ አ.ማ. ቅርንጫፍ በኩል እኩል መጠን ባለዉ በጥሬ ገንዘብ ሊወሰድ የሚችል ነው፤

**"የዉጪ ዜጋ"** ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው ሰው ማለት ነው ምንም እንኳን ይህ ሰው ኢትዮጵያዊ ውስጥ በቋሚነት ቢኖርም ባይኖርም፤

**"የመዝገብ ደብተር"** ማለት ሁሉም ግብይቶች የተመዘገቡበት ወኪሉ የሚይዘው ደብተር ነው፤ ግብይቶቹ በተሳካ መልኩ ለመከናዎናቸው እንደበቂ ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል፤.

**"ኤም-ብር አገልግሎት"** ወይም **"ኤም-ብር"** ማለት በ አብቁተ አ.ማ. የሚቀርብ የሞባይል ገንዘብ አገልግሎቶች ማለትም ገንዘብ ማስተላለፍ ፤ ማስቀመጥ፤ወጪ ማድረግ እና ሌሎች ተዘማጅ አገልግሎቶችን ነው፤

**"ኤም-ብር ስርዓት"** ወይም **"ኤም-ብር"** ማለት የኤም-ብር አገልግሎቶችን በሚያቀርበው አብቁተ አ.ማ. የሚተገበር ስርዓት ማለት ነው፤

"አብቁተ አ.ማ. **ቅርንጫፍ** " ወይንም "አብቁተ አ.ማ. **ንዑስ ቅርንጫፍ"** ማለት ለደንበኛ የቀረበ አብቁተ አ.ማ.ማለት ነው፤

**"አብቁተ"** ማለት ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ማለት ነው፤

**"ኔትዎርክ"** የኢትዮ ቴሌኮም በፌዴራላዊ ዲሞክሪያሲያዊ ኢትዮጲያ ውስጥ የዘረጋው የሞባይል ግንኙነት ኔትዎርክ ማለት ነው፤

**"የሱቅ ኦፕሬተር"** ማለት እርስዎን በወኪሉ ሱቅ የሚያስተናግድ ነው ፤

**"ሱቅ"** ማለት በወኪሉ የሚተዳደር ማንኛውም ዐይነት ሱቅ፣ ክፍል ወይም የችርቻሮ ቅጥር ግቢ ወይም ክፍል ነው፤

**"ተሳትፊ"** ወይም **"ተጠቃሚ"** ማለት የኤም ብር አገልግሎቶችን በመጠቀም ብርን ለመላክ ወይም ለመቀበል በኤም ብር ስርዓት ውስጥ የሚካፍል ሰውን ማለት ሲሆን ይህም የኢ-ገንዘብን አሰባስብን ያመቻችን ሰው ይጨምራል፤

**"ፒን"** የግልዎት የሆነ መለያ ቁጥር ሆኖ የራስዎን አካዉንት ለመግባትና ለማስተዳዳር የሚመርጡት የይለፍ ቃል ማለት ነው፤

**"ቅድመ-ክፍያ የአየር ግዜ"** በኢትዮ ቴሌኮም ያለ የሞባይል መደወያ ሒሳብ ማለት ነው፤

**"የመመዝገቢያ ቅጽ"** ማለት የመመዝገቢያ ዝርዝሮችን የያዘ እንዲሁን የርስዎን እነዚህን ውሎችና ሁኔታዎች መቀበል የያዘ ቅጽ ነው፤

**"ሴት-ኣፕ ፒን"** ማለት በምዝገባ ወቅት አካዎንቶን ለማክፈት አላማ ሲባል የሚላክልዎት የአንድ ግዜ ባለ አራት ቁጥር ፒን ነው፤

**"ሲም ካርድ"** የተጠቃሚዉ የመለያ መንገድ ሆኖ ከትክክለኛ የሞባይል ስልክ ጋር ሲጠቀሙት በኢትዮ ቴሌኮም የሞባይል ኔትዎርክ ላይ የስልክ ጥሪ ለማድረግ እና የኤም-ብር አገልግሎቶችን ለመጠቀም የሚያስችልዎት ማለት ነው፤

**"ኤስ.ኤም.ኤስ"** ማለት አጭር የስልክ መልዕክት መላላኪያ አገልግሎት ሆኖ የጹሁፍ መልዕክቶችን ከአንድ ሞባይል ስልክ ወደሌላው ለመላክ የሚያስችል ነው፤

**"ግብይት"** ለኤም ብር አገልግሎት በተመዘገበ ሰው ወደ ኤም-ብር ስርዓት የሚደረግ ማንኛውም ጥያቄ ወይም እንደ ተመዘገበ ተጠቃሚ በደንበኞች አገልግሎት ማዕከል የሚሰጥ አገልግሎት ማለት ነው። ወደ ደንበኛ የኤም-ብር አካውንት የሚደረግ ገቢ ወይም ወጪ እንቅስቃሴን ጨምሮ።

**"እርስዎ"** ወይም **"የርስዎ"** ማለት የኤም-ብር አገልግሎትን ለመጠቀም የተመዘገበ የኤም-ብር ደንበኛ ማለት ነው፤

# የአገልግሎት ገለጻ

2.1. ማፋተ እርስዎን እንደደንበኝነት በተመዘገበ የሞባይል ስልክ ወይንም በሌላ አማራጭ ገንዘብን ለመላክ ሆነ ለመቀበል የሚያስችልዎትን የኤም-ብር ሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ይተገብራል፤ የኮርፖሬት ደንበኞችን አያካትትም፤

2.2. ኤም-ብር ለሁሉም በኢትዮ ቴሌኮም ለተመዘገቡ የስልክ ባለቤቶች እና ስልክ ለሌላቸው ተጠቃሚዎች እነዚህ የቀረቡትን ውሎችና ሁኔታዎችን ተቀብለው ለኤም-ብር አገልግሎቶች ለሚመዘገብ ሁሉ የቀረበ ነው፤

2.3.. የኤም-ብር አካውንት የ ግል ምዝገባን ኤም-ብር ወኪል ዘንድ ወይንም በተሳታፊ ማፈተ ቅርንጫፍ በመቅረብ የኤም-ብር የምዝገባ ቅጹን በመሙለት ማከናወን ይቻላል፤ ነገር ግን ለ ኮርፖሬት አካውንት ደንበኝነት ምዝገባ በአካል ወደ ማፈተ ቅርንጫፍ ሄዶ መመዝገብ ይኖርበታል፤

2.4. የኤም-ብር አገልግሎትን ለመጠቀም ሲመዘገቡ ለቀረቡት ውልና ሁኔታዎችን ይስማማሉ፤( "ውልና ሁኔታዎቹ") በእርስዎና በ አብቁተ አ.ማ.መካከል የህግ ዉጤት ያለው ስምምነት ይፈጥራል፤

2.5. ማፈተ አ.ማ.በራሱ ነጻ በሆነ ስልጣኑ በኤም-ብር ስርዓት ውስጥ መመዝገብን መከልከል ሆነ የተመዘገበውን ሰው መሰረዝ ይችላል፤

2.6. የኢ-ገንዘብን ጥሬ ገንዘብ በኤም-ብር ወኪል ወይም ቅርንጫፍ ኣዉትሌት በማስቀመጥ ሊያገኙ ይችላሉ ወይም የኢ-ገንዘብ ሃዋላ ከሌላ የኤም-ብር ተጠቃሚ ወይም አለም አቀፍ ከሆነ የሃዋላ ገንዘብ ከተሳታፊ የሃዋላ አገልግሎት አቅራቢ እንዲሁም አብቁተ አ.ማ. ከሚያቀርበው ተቀባይነት ባለው መንገድ ሁሉ ሊያገኙ ይችላሉ

2.7. ሁሉም ግብይቶች የሚሰፈሩት በኢትዮጵያ ብር ነው፤

2.8. የግብይት መጠን ውስንነት እና ውልና ሁኔታዎችን አንቀጾች ተግባራዊ ሆነው ፤ ቀሪ የኤም-ብር አካዎንቶ በማናቸውም ግዜ ሊቤዡት ይችላሉ ሊወገድ የሚችለውም በኤም-ብር ስርዓት ውስጥ እርስዎ በሚያስተላልፉት ትእዛዝ መሰረት ብቻ ነው፤

2.9. ለኤም-ብር አገልግሎት ተግባራዊ የሚሆኑት ክፍያዎች ተለይተው በዝርዝር በወኪሉ አውትሌት፣ አብቁተ ቅርንጫፎች ይቀርባሉ በየግዜውም በአብቁተ አ.ማ.ይታተማሉ በአብቁተ አ.ማ.በግል ስልጣኑም ለውጦችን ሊያደርግ ይችላል፤

2.10 እኛ ምንም እንኳን የኔትዎርክ ሽፋን ባለበት ቦታ ሁሉ እርስዎ ኔትዎርኩን በመጠቀም ሙሉ የኤም-ብር አገልግሎት አቅርቦት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ብንሞክርም የኤም- ብር አገልግሎት ሁልግዜ ይኖራል ብለን ዋስትና አንሰጥም እንዲሁም በኤም-ብር አገልግሎት ባለመገኘቱ ምክንያት ለሚከሰቱ ማናቸውም አይነት ኪሳራዎች ሃላፊነት የለብንም። የኤም ብር አገልግሎቶች እንከን አልባ አይደሉም ስለዚህ አንድ አንድ ሁኔታዎች(ሌሎች ተጨማሪ እንዳሉ ሆነው) ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች፤የጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ፤የአየር ንብረት ሁኔታ ፤ በኔትዎረኩ ላይ የታቀዱ የጥገናና የማሻሻያ ስራዎች በኤሜ-ብር አገልግሎት አቅርቦት እና ጥራት ላይ አሉታዊ የሆነ ጣልቃ ገብነት ያመጣሉ።

2.11 ሲም ካርድ በተበላሸ፤በጠፋ ወይም በተሰረቀ ጊዜ መበላሸቱን፤ መጥፋቱን ሆነ መሰረቁን በአቅራቢያዎት ያለውን ወኪል ወይም ቅርንጫፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበዎት። እነርሱም ከደድም ጋር ያገናኝዎታል ሲሙ እስከሚተካልዎት ድረስ ሌላ የኤም ብር አገልግሎትን ለመከልከል ሲባል አካዎንትዎ ለጊዜው ይታገዳል። የአካዉንት ጊዜያዊ ዕገዳ እና የድጋሚ መክፈቻ ክፍያ ይኖራል እርስዎም ለዚህ ክፋያ ሃላፊነቱን ይወስዳሉ፤እንዲሁም የመበላሸቱን፤ የመጥፋቱን ሆነ የመሰረቁን ማስታዎቂያ እስከደረሰን ድረስ ላለው ግብይት ክፍያዎች እርስዎ ሃላፊ ይሆናሉ። የመበላሸቱን፤ የመጥፋቱን ሆነ የመሰረቁን ማስታዎቂያ እስኪደረሰን ድረስ ባለው ግዜ በስልክዎ እና በሲሙ ለተከናወነ ግብይት ለሚነሳ የይገባኛል ጥያቄ እርስዎ ዋስትና እንዲሰጡን ይጠየቃሉ።

2.12 በየግዜው ስለኤም-ብር አገልግሎትን በተመለከተ የምንሰጠዎትን መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ።

2.13 ወደ ደድማ የሚያደርጉአቸው ጥሪዎች ለንግድ አሰራር ጠቀሜታ ሲባል ይቀረጻሉ ወይም ቁጥጥር ይደረግባቸዋል ማለትም ጥራትን ለመቆጣጠር፤ ስልጠና፤ ስኬታማ የሆነን የስርዓት አሰራርን ለማረጋገጥ፤ የቴሌኮምንኬሽን ሲስተማችንን ካልተፈቀደለት አጠቃቀም ለመከላከል እና ወንጀልን ለመከላከል።

# ክፍያና ታሪፍ

3.1. ለሚኖሩት የክፍያ አይነቶች እርስዎ ሃላፊ ይሆናሉ። የታሪፉ መመሪያ ከ አብቁተ አ.ማ.ዋና ቢሮ ፤አብቁተ ቅርንጫፍ ፤ ከወኪል ሱቅ እና ከ ኤም-ብር ደረገጽ ይገኛል። ተግባረዊ በሚሆነው ዋጋ ላይ ጥርጣሬ ቢኖረዎት የኤም-ብር ወኪሎች ኔትዎረክ እና አብቁተ ቅርንጫፎች በዋጋ ተመኑ ላይ ሊያግዝዎት ዝግጁዎች ናቸው።

3.2. በእያንዳንዱ ግብይት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ክፍያ ከኤም-ብር አካዎንት ላይ ግብይቱ በተከናወነ ግዜ ይቀነሳል።አዲሱ ቀሪ ሂሳብዎት ስልክ ካሎት በኤስ ኤም ኤስ ይደርስዎታል።

3.3. በሌላ መልኩ ካልተገለጸ በስተቀር ክፍያዎቹ ሁሉንም የግብር አይነቶች ያጠቃለሉ ናቸው።

## ለአካዉንት ማመልከቻ

4.1 ማንኛውም አካውንት ለመክፈት ህግ የሚፈቅድለት ሰው የኤም -ብር አገልግሎትን ለማግኘት አካውንት መክፈት ይችላል። የርስዎ የሆነ የኢትዮ ቴሌኮም ሲም ካርድ ካለሆት ስልክ ቁጥሩን ከአካውንቱ ጋር በማያያዝ የኤም ብርን አገልግሎት በስልክሆ ማግኘት ይችላሉ።

4.2 የኤም -ብር አካዉንት በስም ለመክፈት ቢያንስ ቢያንስ እድሜ 18 አመት መሆን እና ውል የመግባት ችሎታ ሊኖረው ይገባል።

4.3 አገልግሎት በ ኤም-ብር ወኪል ወይም በፌዴራላዊ ዲሞክሪያሲያዊ ኢትዮጲያ ውስጥ በተሳታፊ አብቁተ ስም ቅርንጫፍ መመዝገብ ይቻላሉ።

4.4 መመዝገቢያ ቅጹን እርስዎ ሞልተውን ፈረመው ማቅረብ ይኖርብዎታል።ጥርጣሬን ለማስወገድ ይረዳ ዘንድ በመመዝገቢያ ቅጹን ላይ ስምዎ በመታዎቂያ ደብተሩ ላይ እንደሰፈረው መጻፍ አለበት። በተጨማሪም የሚከተሉት መረጃዎች መኖር አለበት፡

- የመታዎቂያ ደብተር ቁጥር
- የመኖሪያ አድራሻ
- የትዉልድ ቀን
- ዜግነት
- የስልክ ቁጥርዎ
- የእናትዎ ስም

4.5 በቂ የሆነ የማንነት መታወቂያ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርብዎታል።. ለዚህ ስምምነት አላማ ሲባል ኢትዮጵያዊ ከሆኑ፤ በቂ የሆነ የማንነት መታወቂያ ማስረጃ ማለት ኦርጂናል የቀበሌ መታዎቂያ ካርድ፤ ግዚያዊ የቀበሌ መታዎቂያ ካርድ፤የገበሬዎች ማህበር መታዎቂያ ካርድ፤ ወይንም ፓስፖርት፤ለአንድ ፕሮግራም የተዘጋጀ መታወቂያ ፤የዉጪ ሃገር ዜጋ ወይም የተመዘገበ ዲያስፖራ ከሆኑ ደግሞ ኦርጂናል ፓስፖረት ፤ የመኖሪያ መታዎቂያ ካርድ ፤ የተማሪ መታወቂያ ፤ ወይንም መንጃ ፈቃድ ። የመታዎቂያ ካርዶቹ ኮፒ ምዝገባዉን ለሚያመቻች ወኪል መቅረብ አለባቸው። በተጨማሪ ለ ንግድና ለ ኮርፖሬት ደንበኞች ኦሪጅናል የንግድ ፍቃድ ፤ ቲን ሰርተፊኬት እና የቫት ተመዝጋቢ ሰርቲፊኬት (እሚመለከተው ከሆነ) ከ ኮፒው ጋራ መቅረብ አለበት።

4.6 የቀረቡት መረጃዎች ሙሉና በሁሉም አቅጣጫ ትክክል መሆን አለባቸው።

4.7 የመመዝገቢያ ዝርዝሮቹ የጊዜው መሆናቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለብዎት።

4.8 የመመዝገቢያ መስፈርቶቹ ካልተሟሉ ወይም አጥጋቢ ያልሆነ የማንነት መታዎቂያ ካቀረቡ አብቁተ አ.ማ.የምዝገባ ማመልከቻዎትን በገዛ ስልጣኑ ሊከልክል ይችላል ።

4.9 ስልክ ካሎት አካዎንትዎ የሚት ዐፐ ፒን ከተከፈተ በኋላ የሚስጥር ፒን በመምረጥ ወዲያዉኑ የኤም-ብር አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

4.10 በኤም-ብር አካውንት ወስጥ ላለ ገንዘብ ምንም አይነት ወለድ አይከፈለም።

4.11 አብቁተ አ.ማ. በማናቸውም ጊዜ አካውንቶን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፤ በዚህ ጉዳይ ላይ አለመተባበር የኤም-ብር አገልግሎት አጠቃቀም ላይ ገደብን፤የአካዎንቱን መታገድ ወይም መሰረዝን ያስከትላል።

4.12 በአንድ የሞባይል ቁጥር ከአንድ በላይ የ ኤም-ብር አካዎንት ሊኖርዎት አይችልም።

4.13 ከላይ የተጠቀሰው ጠቅላላ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ የወላጅ ስልጣን ያለው ሰው አቅመ ችሎታ ላልደረሰ ሰው መያዝ ይችላሉ። ለዚህ ስምምነት አላማ የወላጅ ስልጣን ያለው ሰው ማለት ለአቅመ መጠን ላልደረሰ ሰው ወላጆች፤ የህግ ሞግዚትን፤ የትምህርት ቤት ኃለፊን ወይንም ለአቅመ መጠን ላልደረሰ ሰው ጉዳዮች ላይ ህጋዊ ስልጣን ያለውን ሰው ያመለክታል።

## የኤም-ብር አቅርቦት ኃላፊነት

5.1. የኤም-ብር አገልግሎቶች አቅርቦት በፒን የተከለከሉ ናቸው። ስለዚህ እርስዎ ፒን ቀጥሩን ለመጠበቅና ሙሉ የፒን ቁጥሩን ለሶስተኛ ወገን ላለማሣይት ይስማማሉ፡ሶስተኛ ወገን እነዚህን ይጨምራል የኤም-ብር ሱቅ ሰራተኞች፤ የ አብቁተ አ.ማ.ሰራተኛ፤ የኤም-ብር ሰራተኛ ወይም ፒን ቁጥሩን ለማወቅ ስልጣን እንዳለው የሚሞክር ሰው። ደድማ ሢያነጋግሩ የርሶን መታወቂያ፤ሌላ መረጃውችን እንደ ከፒን ቁጥርዎ ምናልባት አንድ አሃዝ ማንነትን ለማጣራት እንጠቀማለን ሆኖም ግን <u>ሙሉ</u> የፒን ቁጥርዎትን ለደንበኞች ድጋፍ ማዕከል ሠራተኛ እንኳን ቢሆን እንዳይሠጡ።.

5.2. ለፒን ና ለሚስጥር ቃል ደህንነት እርስዎ ብቻ ሃላፊነት እንደሚወስዱ እውቅናን ይሠጣሉ። አብቁተ አ.ማ.ለፒን ቁጥርዎት መጋለጥ ሃላፊነት የለበትም ስለዚህ እርስዎ የፒን ቁጥርዎ ከመጋለጥ የተነሳ ለሚደርስብዎ ጉዳት የአብቁተ አ.ማ. ስምን ከጉዳት ይጠብቃሉ።

5.3. ለ አብቁተ አ.ማ.ለሚሰጡት ለሁሉም ትዕዛዞች ሃላፊ ይሆናሉ።

5.4 አብቁተ አ.ማ. ትክክለኛ የሆነ የፒን አግባብን በህጋዊ የኤም-ብር አካውንት ባለቤቱ እንደተከናወነ ይገምታል ስለዚህ ሁሉንም ተከታታይ ግብይቶች በትክክል በርስዎ እንደተፈጸሙ ይወስዳል።

5.5 የኤም-ብር አገልግሎቶችን በኢትዮጵያን ህግ ላይ ወንጀልን ለመፈጸም መጠቀም አይችሉም።

## ተቀባይነት ያለው የአካዎንት አጠቃቀም

6.1. አካዎንቶ ተከፍቶ ስራ ሲጀምር እነዚህን ተግባሮች ማከናወን ይችላሉ፡

6.1.1; ኢ-ገንዘብን በተሳታፊ ወኪል ሱቅ ማስቀመጥ፤

6.1.2 ለሌሎች ኢ-ገንዘብን መላክ ከሌሎች ተጠቃሚዎች ኢ-ገንዘብን መቀበል፤

6.1.3; ጥሬ ገንዘብን ከአካዎንትዎ ዉስጥ በኤም-ብር ወኪል እና በቅርንጫፎች አማካኝነት ወጪ ማድረግ (ቅርንጫፍ ለ ኮርፖሬት ደንበኞች ብቻ)።

6.1.4 የኢትዮ ቴሌኮም ቅድም ክፍያ የአየር ሰዓት መግዛት (ኮርፖሬት ደንበኞችን አይመለከትም)፤

6.15 ወደ ብድር አካዎንቶ ገንዘብን መላክ (ካለ)

6.1.6 አካዎነቶን ማስተዳዳር (ለምሳሌ ቀሪ ሂሳብን ማጣራት፤ፒን መቀየር ወዘተ.); እና

6.1.7 ከግዜ ወደ ግዜ በ አብቁተ አ.ማ. ወይንም በፋይናንስ ተቋማት የሚተዋወቁ ሌሎች ተግባሮች

6.2. አብቁተ አ.ማ. ሁሉም ሊተገበሩ የሚችሉት ነገሮች ሁሌ ይኖራሉ የሚል ዋስትና አይሰጥም። አንዳዶቹን ወይንም የኤም-ብር አገልግሎትን በጠቅላላ ቀጥተኛ በሆነ የህግ መሻሻል ፤የመንግስት ደንብ ወይም ፖሊሲ ውጤት ሊያነሳ ይቻላል።

## እገዳ፤ ማቋረጥ፤ ማገድ እና ያልተፈቀደ አጠቃቀም .....

7.1. አብቁተ አ.ማ.ካለምንም ሃላፊነት በገዛ ስልጣኑ ካለምንም አየነት ሃለፊነት ስምምነቱን የማገድ ወይም የመሰረዝ መብት አለው ቀጥሎ ሁኔታዎች ግዜ፡

- የኤም-ብር አካዎንትን ባልተፈቀደ፤ህገወጥ፤አግባብ በሌለው መልኩ፤ለመጭበርበር ወይም ለወንጀል ስራ ከተጠቀሙበት
- ይህን የአጠቃቀም ሁኔታ ጨምሮ ለኤም ብር አገልገሎት የተሰጡትን ቅደመ ሁኔታዎች ካለከበሩ
- ፒን ቁጥርዎ እንደ ጠፋ ወይንም ፒን ቀጥሩን ሌላ ሰው እንዳወቀዉ ሲያሳዎቁን (ወይንም የስልክ ቀፎ ከተሰረቀ ወይም ከጠፋ)
- በሞባይል ሥልክዎ የኤም-ብር አገልግሎቱን ወይም የኔትዎርክ ደህንነቱን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም ስራዉን የሚያደናቅፍ ነገር እንዲሆን ካደረጉ(እንዲሆን ከፈቀዱ)
- ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች;

7.2 አካውንቱ እንዲዘጋ ጥያቄ ባቀረቡልን ግዜ አካዉንቱን እንዘጋለን።

7.3. አብቁተ አ.ማ.በህግ ተገዶ አካውንቱን ሊያግድ ወይም በቂ በሆኑ ምክንያቶች አካዎንቱ ከወንጀል፤ከአሸባሪ ወይም ከማጭበርበር ጋር ተያይዞ ብር መቀበል ወይም መላክን ከጠረጠረ ያዘዙትን የግብይት ጥያቄ ውድቅ ሊያደርግ ይችላል።

7.4. አብቁተ አ.ማ.ማስታወቂያዎችን በፖስታ አድሻዎት ወይም በአየመ በኤም-ብር ስርዓት ውሥጥ ወደ ተመዘገበው ሞባይል ቁጥርዎት ይልክ ይሆናል።

7.5 ይህ ስምምነት የኤም ብር ተመዝጋቢው በሞተ ግዜ ወዲያዉኑ ይቋረጣል።

## ግብይቶች

**8.1 ኢ-ገንዘብ ማስቀመጥ**

8.1.1 ኢ-ገንዘብ በቀጥታ ማስቀመጥ የሚችሉት ወደራሥዎ ኤም-ብር አካዉነት ብቻ ነው፤ ወደሌላ ሰው የኤም-ብር አካዉንት ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ይቻላሉ

8.1.2. ኢ-ገንዘብ ለማስቀመጥ፤ የተጠየቀውን መረጃ መሙላት ይኖርብዎታል፤የአካዉንቱ ባለቤት መሆንዎን ለማጣራት የማንነት ማጣሪያዎችን ማስተላለፍ፤እንዲሁም ለኤም-ብር ኤጀንት ወይንም በ አብቁተ አ.ማ.ቅርንጫፍ ማስቀመጥ ካሰቡት ኢ-ገንዘብ ጋር እኩል የሆነ ጥሬ ገንዘብ መስጠት ይኖርብዎታል።

8.1.3. ጥሬ ገንዘቡን ለኤም-ብር ወኪል/ቅርንጫፍ ከሰጡ በኋላ እርስዎ እና ወኪሉ/ቅርንጫፉ የመዝገብ ደብተሩን መፈረማችሁን እና ደረሰኝ መቀበልዎትን ማረጋገጥ ይኖርብዎታል ይህም የማስቀመጥ ግብይቱን እንዳጠናቀቃችሁ በቂ ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል፡፡

8.1.4. አብቁተ አ.ማ.የግብይት መጠንን ለመገደብ እና ለተወሠኑ የኤም ብር አካዉንቶች ከፍ ያለ ወይም ዝቅ ያለ መጠን የመስጠት መብቱ የተጠበቀ ነው ፡፡

## 8.2 **ኢ-ገንዘብ ማስተላለፍ**

8.2.1 በአብቁተ አ.ማ.የሚወሰኑት የግብይት መጠንና የክፍያ ተመን በእያንዳንዱ“ የገንዘብ ዝውውርን” ወይንም ሌሎች ክፍያን ከአካዎንትዎ የሚፈጽሙ ግልጋሎቶችን በተጠቀሙ ግዜ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

8.2.2 የግብይት ጥያቄዎት የማይፈጸመው፡

- በኤም-ብር አካውነት ውስጥ ግብይቱን ለማከናወን ያሚያስችል ወይም የግብይቱን ክፍያ ለመሸፈን በቂ ሂሳብ ከሌለ;
- ተቀባዩ የተፈቀደለተን የአካውንት ጣራ መጠን ከደረሰ;
- በአብቁተ አ.ማ.የተሰጠውን የቀን የዝዉዉር መጠን ከተጠቀሙ;
- ተቀባይነት ባላቸው ምክንያቶች የርስዎ አካዉንት ለጊዜዉ ከታገደ ወይንም ለዘለቄታው ከታገደ ;
- ሌላ አስገዳጅ ምክንያት ሲኖር እንደ ጊዜያዊ የሲስተም መዘግየት፡፡

8.2.3 ኢ-ገንዘብን የኤም-ብር ሜኑ መመሪያዎችን በመከተል ለሌላ የኤም-ብር ተጠቃሚ ወይንም ላለተመዘገበ የኢትዮ ቴሌኮም ሲም/ ቀፎ ላለው ተጠቃሚ መላክ ይችላሉ (የኮርፖሬት ደንበኞችን አይመለከትም)፡፡

8.2.4 ለሚፈጽሙት ማናቸውም ግብይት ዋጋ ይከፍላሉ፡፡ የክፍያዉ መጠን ታትሞ በወጣው ታሪፍ መሰረት ይሆናል፡፡

8.2.5. ኤም-ገንዘቡ በኤም-ብር አካውነት ውስጥ ግብይቱን ለማከናወን ያሚያስችል ( የግብይቱን ክፍያ ለመሸፈን) በቂ ሂሳብ ከሌለ ግብይቱ አይከናወንም፡፡ ምንም ኢ-ገንዘብ ከ ኤም-ብር አካዎንት ውስጥ ተቀናሽ አይሆንም፡፡

8.2.6 ወደሌላ ወገን ያደረጉት ግብይትዎ ከተሳካ፣ አብቁተ አ.ማ. ወዲያዉኑ ለተላላፈለት ሰው የኤም-ብር አካዉንት ይታላለፋለታል፡፡ የተላከለት ሰውና እርስዎ በአጭር የስልክ መልክት ስለተጠናቀቀው ግብይት እንዲያውቁ ይድረጋል፡፡

8.2.7. አብቁተ አ.ማ. ግብይቱን ማጠናቀቅ ካልቻለ በአጭር የስልክ መልዕክት ግብይቱ ያልተጠናቀቀበትን ምክንያት እንዲያወቁ ይደረጋል፡፡

8.2.8. የሚያከናውንቱ ግብይት ለራስ በተለየ የግብይት ቁጥር ይኖረዋል ይህም ቁጥር በሚላክልዎት የማረጋገጫ አጭር የስልክ መልዕክት ውስጥ ይኖራል ከዚህ ጋር አብሮ የትክክለኛ ቀሪ ሂሣብ መጠን ይካተታል፡፡

8.2.9. የተሳካ የኢ-ገንዘብ ዝውውር ከአካውንቶ ወደ ተመዘገቦ የኤም-ብር አካውንት ተቀባይ በተከናወነ ግዜ የኢገንዘብ ባለቤትነት ለተቀባዩ ይሆናል፡፡

8.2.10. ተቀባዩ በኤም-ብር ሰርዓት ውስጥ ያልተመዘገበ ከሆነ የኢ-ገንዘብ ባለቤትነት ከእርስዎ ጋር ይሆናል፡፡ ነገር ግን ገንዘቡን መልሰው መውሰድ ሆነ ገንዘቡን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይንም ግብይቱን መመለስ አይችሉም፡፡ ሊመለስ የሚችለው ግን የመጀመሪያው ግብይት በአንቀጽ 8.2.12. በተጠቀሰው የግዜ ገደብ መሠረት ተቀባይ የተላከለትን ብር ካልወሰደ ነው፡፡

8.2.11. ለተቀባዩ የኤም -ብር አካዉንት ከሌለው አብቁተ አ.ማ. የአንድ ግዜ ደረሰኝ የያዘ አጭር የስልክ መልእክት የገንዘብ መቀበያ ኮድ አያየዞ ይልክለታል፡፡ ይህም የተላከለትን ገንዘብ አንዲቀበል ያስችለዋል፡፡

8.2.12 . በ15 ቀናት ውስጥ ወይንም አብቁተ አ.ማ. በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ላልተመዘገበ ተቀባይ የተላከው ገንዘብ ተቀባዩ ወደ ጥሬ ገንዘብ ካላስቀየረ፤ አብቁተ አ.ማ. ግብይቱን ይሰርዝና ኢ-ገንዘቡ ወደ አካውንቶ ይመለሳል፡፡ የገንዘቡን መመለስና የግብይቱ መሰረዝ የሚገልጽ አጭር የስልክ መልእክት ይደርስዎታል፡፡

8.2.13 የተከናወነ ግብይት የመጨረሻና የማይሰረዝ ነው ሰለዚህ አብቁተ አ.ማ. የተከናወነውን ግብይት የመቀልበስ ግዴታ የለበትም፡፡

8.2.14 ከላይ የተጠቀሰው 8.2.13 ቢኖርም አብቁተ አ.ማ. በራሱ ስልጣን ግብይቱን ሊቀለብስ ይችላል፡፡ በቂ የሆኑ ምክንያቶች በኖሩ ጊዜ ማለትም ግልጽ የሆነ ስህተት፤ማጭበርበር ከታየና ተቀባዩ ኢ-ገንዘቡን ካልወሰደ እንዲሁም የይመለስልኝ ጥያቄው የተሳሳተ ግበይቱ ከተፈጸመ በአንድ ወር (1) ግዜ ወስጥ ከቀረበ፤

8.2.15 አብቁተ አ.ማ. ኢ-ገንዘቡ ለተቀባዩ በስህተት ሆነ መባጭበርበር ወይም በአዕምሮ ጫና ለተከናወነ ግብይት ተቀባዩ ላስመነዘረው ወይም ወጪ ላደረገው ገንዘብ የማስመለስ ወይም የማካስ ግዴት የለበትም፡፡እርስዎ የ አብቁተ አ.ማ. ስምን ለተፈጠረው የስህተት ሆነ የማጭበርበር፡ የአእምሮ ጫና ሆነ በግዴታ፤ በወንጀል ሃይል ምክንያት የተደረገው የገንዘብ ዝውውር ለፈጠረው ኪሳራ ከጉዳት እንደሚጠብቁ ይስማማሉ፡፡

## 8.3 **ኢ-ገንዘብን መቀበል**

8.3.1 እርስዎ በኤም-ብር ስርዓት ውስጥ የተመዝገቡ ከሆነ ከሌላ የኤም-ብር ተጠቃሚ ወይም አለም አቀፍ የሃዋላ ኢ-ገንዘብ ሲቀበሉ መቀበልዎን የሚገልጽ አስመ ይደርስዎታል፤ ኢ-ገንዘቡን ከወኪል ሱቅ ወይም ከ አብቁተ አ.ማ. ቅርንጫፍ ሊቀበሉ ወይንም ለሌላ ሶስተኛ ወገን የኤም-ብር ሜኑ አማራጮችን በስልክዎት ላይ በመጠቀም ገአብቁተ አ.ማ. ገንዘቡን ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

8.3.2 በስህተት ገንዘብ ቢቀበሉ ገንዘቡን ለላኪው የመመለስ ግዴታ እንዳለብዎት እውቅና ይሰጣሉ። ይህ ባይሆን ግን አብቁተ አ.ማ. ክፍያውን ለላኪው ይመልሳል።

8.3.3 በስህተት የተላከሎትን ገንዘብ በመጠቀመዎ በህግ ተጠያቂ ሊሆኑና ክስ ሊመሰረትብዎ ይችላል።

**8.4. ኢ-ገንዘብ ማውጣት (መውሰድ)**

8.4.1. የወኪል ሱቆች እና አብቁተ አ.ማ. ቅርጫፎች፡ በወኪል ወይም በአብቁተ አ.ማ. ቅርጫፍ የሚደረጉትን መመዘኛዎችን ካለፉ በኃላ ወደ አካውንቶ በመግባትና በስልክዎት ላይ ያለውን የኤም-ብር ሜኑ በመጠቀም ኢ-ገንዘብ ሊያወጡ ይችላሉ። ነገር ግን የብር ማውጣት ግብይት መጀመር ያለበት በወኪሉ ቅጥር ግቢ ወይም በአብቁተ ቅርጫፍ መሆን አለበት (የኮርፖሬት ደንበኞችን አይመለከትም)። እንዲሁም የመዝገብ ደብተሩን እንደፈረሙ ማረጋገጥ ይኖርብዎታል፤ ይህም ግብይቱ በተሣካ መልኩ ለመከናወኑ ሙሉ ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል። እንደ ኮርፖሬት ደንበኛ ገንዘብ ወጪ የማድረግ ስነ-ስርዐት ሲፈፀም የሚችለው በአብቁተ ቅርጫፍ ፤ በ ቅርንጫፉ ሰራተኛ ወይም ካሽር ብቻ ነው።

8.4.2. አብቁተ አ.ማ. የግብይት መጠን መወሰንን ከግምት በማስገባት ጠያቂው የማንነት ማጣሪያዎችን ሆነ የደህንነት ማረጋገጫዎችን ካለፈ በኃላ የቀረበውን ጥያቄ ያስተናግዳል። ገንዘብን ለመቀበል ግጭት ቢፈጠር ለአብቁተ አ.ማ. በግብይቱና የሚገባውን ሰው ማንነት ለማጣራትና የደህንነት ማረጋገጫ ሂደቶች መሃል ያለውን የሎጂክ ግንኙነት መኖሩን መሳየት በቂ ነው።

8.4.3. ሌላ ተቃራኒ አንቀፅ ካልኖረ በኤም-ብር አካውንት ገንዘብ ባወጡ ቁጥር ክፍያን ይፈፅማሉ።

## የግላዊነት ፖሊሲ

9.1. አብቁተ አ.ማ.ተጠቃሚዎች የሚያቀርቡትን መረጃ ግላዊነት የመጠበቅ አስፈላጊነትን ያከብራል። ይህ አረፍተነገር ለግላዊነት መብት መከበር ያለንን ትልቅ አክብሮት የሚያንፀባርቅ ነው።

9.2. አብቁተ አ.ማ.የኤም-ብር ተጠቃሚዎችን ዝርዝር ለማያዝ፣ እያንዳንዱን የኤም-ብር አካውንት ለማስተዳደር፣ የኤም-ብር ዳታቤዝ ወቅታዊነት ለመጠበቅ እና ለተገልጋዮች ድጋፍ ለመስጠት የግል መለያ መረጃ ይሰበስባል።

9.3. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እንዳሉ ሆነው፤ አብቁተ አ.ማ.ላልተፈቀደላቸው አካላት መረጃዎትን አያካፍልም፣ መረጃዎችን ካልተፈቀደ አቅርቦት ለመከላከልና የእርስዎን መረጃ ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ይረዳ ዘንድ በቂ የመከላከያ ስራዎች ተግባራዊ ሆነዋል።

9.4. አብቁተ አ.ማ.እና የተፈቀደላቸው የተዋዋዮች ሰራተኞች የእርስዎን መረጃ በሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ የተጣለባቸው ስለሆነ ላተፈቀደለት ሦስታኛ ወገን መረጃዎትን አሣልፈው አይሰጡም። አብቁተ አ.ማ.ለውስጣዊ የመረጃ ደህንነት ሃላፊነት አለው። የአብቁተ አ.ማ.ሰራተኞች የግላዊነት ፖሊሲዎችን ከጣሱ ብዙ አይነት የዲሲፒሊን እርምጃዎች ተግባራዊ ይሆንባቸዋል።

9.5. የህገወጥ ገንዘብ ዝውውር ወንጀልን ለመከላከል፣ ለማጋለጥ ወይም ክስን ለማገዝ አብቁተ አ.ማ.የአካውንቶን አጠቃቀም የመቆጣጠርና መረጃዎትን ለሃገር ውስጥ የህግ አስፈፃሚና መርማሪ ኤጀንሲዎች የመግለጽ መብት አለው።

9.6. አብቁተ አ.ማ.እና የተፈቀደላቸው ተዋዋዮች ከግዜ ወደ ጊዜ አጭር የስልክ መልዕክት የመላክ መብት እንዳላቸው ተስማምተዋል።

## መግለፅና ዳታን መያዝ

10.1. የዳኝነት ስልጣን ባለው አካል ከወንጀልና ህገወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብ አካውንትዎ ውስጥ እንዳለ ከተወሰነ አብቁተ አ.ማ.በአካውንትዎ ውስጥ ያለውን ገንዘብ ከወንጀል የተገኘ ገንዘብን ለመቀበል የህግ እውቅና ላለው ተቋም አሳልፎ ይሠጣል።

10.2. አብቁተ አ.ማ.የግብይት ዳታዎን እስከ ሰባት (7) አመት ድረስ ወይም በሌላ ህግ ወይም ደንብ እስከተፈለገበት ግዜ ይዞ ሊቀር ይፈልጋል።

## ዋቢዎች እና የሃላፊነት መወሠን

12.1. አብቁተ አ.ማ.የተጠራጠረውን የአካውንት እንቅስቃሴ በህገወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብ ሪፖርት ማድረጊያ ቢሮ (ህመገሪቢ.) ሪፖርት ያደርጋል። ህመገሪቢ. የተጠራጠረውን እንቅስቃሴ አግባብ ላለው የህግ አስፈፃሚ ባለስልጣን ማስተላለፍ ይችላል።

12.2. ሁሉም የግብይት ጥያቄዎች በግዜ እንዲከናወኑ አብቁተ አ.ማ. የተቻለውን ሁሉ ያደርግል። ነገር ግን አብቁተ አ.ማ. ለቀጣይ፤ ላልተቋረጠ እና ለአስተማማኝ የኤም-ብር አገልግሎት ከ አብቁተ አ.ማ. ቁጥጥር ዉጪ በሆኑ ጉዳዮች ተጽዕኖ ሊፈጠር በሚችል ወይንም በየጊዜዉ በሚደረግ ፋተሻ፤ እድሳት፤ ጥገና ወይም ማሻሻል ምንም አይነት ዋቢነት አይሰጥም።

12.3 አብቁተ አ.ማ. በራሱ አውቆ ባደረገዉ ጥፋት ካልሆነ በስተቀር ለምንም አይነት የይገባኛል ጥያቄ ሃላፊነት የለበትም ። አብቁተ አ.ማ. የሚከተሉትን ሃላፊነት ወይም የካሳ ጥያቄ ያቃወማል፡፡ ሌሎች ተጨማሪ እንዳሉ ሆነው ፤ ቀጥተኛ፤ ቀጥተኛ ያልሆነ፤ ውጤት ተያያዥ ወይንም ፒዩንቲቭ ካሳ በነዚህና በተገመተ ወይም ይሆናል በተባለ መንስኤዎች፤

12.3.1. ላልታሰበ ተቀባይ የተደረገ ግብይት ወይም በርስዎ የተሳሳተ ገንዘብ መጠን አሞላል ለተከሰተ ግብይቶች

12.3.2. ከራስዎ አካውንት ሁሉንም የማንነትና የማረጋገጫ ፍተሻዎች ባለፈ በሶስተኛ ወገን በተደረጉ ግብዮቶች

12.3.3 ማናቸውም ማጭበርበር ሆነ ማታላል በማናቸውም የኤም-ብር ተጠቃሚ፤ ተጠቃሚው ቢፈተሽም ባይፈተሽም

12.3.4 ከተቀባዩ በሆነ ያለመቀበል ውሳኔ ወይም እርስዎ ያደረጉትን የግብይት በኤም-ብር ስርዓት ውስጥ ያለምመዝገብዎ ለሚያደርሰው ጉዳት

12.3.5. ከኤም-ብር ስርዓት ያልሆነ ሌላ የቴሌኮምንኬሽን ወይም የዳታ ዝውውር ብልሽት

12.3.6. ከመንግስት ሆነ ከባለስልጣን ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ክስተት የሚፈጥረው ውጤት

12.4. የአብቁተ አ.ማ. ሃለፊነት ቢበዛ ለአንድ ወይም ለተከታታይ ክስተት ከነበረዎት ቀሪ ሂሳብ አይበልጥም

12.5 እርስዎ በሶስተኛ ወገን በተነሱ ጥያቄዎች እንዚህን ውልና ሁኔታዎች ባለማክበርዎ የአብቁተ አ.ማ.ን ለመካስ ወይም ከጉዳት ለመጠበቅ ይስማማሉ

## ጠቅላላ

13.1. የራስዎን የኤም-ብር አካውንት በመጠቀም የኤም-ብር ግብይት ለሌላ ሰው ማድረግ ክልክል ነው፤ ለወንጀል ሃላፊነትም ይዳርጎታል፡፡

13.2. እነዚህ ውልና ሁኔታች ሊሻሻሉ፣ሊቀየሩ ወይም ሊለዋወጡ እንደሚችሉ እውቅና ይሰጣሉ፡፡ ወይንም አግባብ ካለው ህግ ወይም ደንብ የሚጣረሱ ሆነው በተገኙ ጊዜ የተቀሩት አንቀፆች ተቀባይነት እና ተፈፃሚነት በማይነካ መልኩ ይሆናል፡፡

13.3. እነዚህ ውል እና ውኔታዎች በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ለተዋዋዮቹ ስምምነት ይሆናሉ፤ የቀድሞ ውልና ሁኔታዎችን ተክተው ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ አዲሶቹና በነባር ውልና ሁኔታዎች መካከል ልዩነት ቢኖር ይህ ትርጉም የበላይ ይሆናል፡፡

13.4. እነዚህ ውል እና ሁኔታዎች በአብቁተ አ.ማ. ከጊዜ ወደ ጊዜ አዳዲስ የኤም-ብር ግልጋሎቶችን ባስተዋወቀ ጊዜ ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡ የተሻሻሉትም ውልና ሁኔታዎች በፖስተር፣በበራሪ ወረቀት፣ በወኪል ሱቆች፣ቅርጫፎች፣በጋዜጣ እና ወይም ኤም-ብር ድህረ ገፅ ሊታተሙ ይችላሉ፡፡ተፈፃሚነታቸውም ከታተሙበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

13.5. የአብቁተ አ.ማ. በዚህ ውልና ሁኔታዎች የተጠቀሱትን መብቶች ያለመጠቀሙ መብቱን እንደተወ አያስቆጥረውም፡፡ በማናቸውም ጊዜ መብቶቹን ከመጠቀም የሚገድበው ነገር አይኖርም፡

13.6. በዚህ ስምምነት የሚኖርዎትን መብትም ሆነ ግዴታ ካለአብቁተ አ.ማ.በፅሁፍ የሆነ ፍቃድ በስተቀር ማስተላለፍ አይቻልም፡፡

13.7. የኤም -ብር አገልግሎትን እነዚህን (ሌሎችንም መጨመር እንዳለ ሆኖ) ለመሰሉ አገልግሎቶች ሆነ ቁሳቁስ ክፍያ ለመቀበል መጠቀም ክልክል ነው፤የዕፅ መድኃኒቶች፣ የጦር መሳርያ፣ የፖርኖግራፊ አገልግሎት ወይም ማቴሪያል፣ ለፒራሚድ ኔትዎርክ አገልግሎት፣ የሶስተኛ ወገንን የአይምሮ ንብረት መብት ለመጣስ፣ ህገ ወጥ ቁማር፣ ሞራልን የሚፃረር ማቴሪያል፣ ስርዓት አልበኝነትን የሚቀሰቅስ ወይም ጉዳት ማድረስን የሚያነሳሳ፣ ከመጠን ያለፈ ፍርዓት እና ጭንቀትን የሚፈጥር፣ ሰዎችን ጊጂ የሆነ ተግባር ወይም ነገርን እንዲጠቀሙ የሚያበረታታ፣ የብሄር፣ የጎሳ ግጭት የሚያነሳሳ፣ የዘር ወይም የሃይማኖት አለመቻቻል የሚቀሰቅስ፣ አደገኛ እና መጠነ ሰፊ ወንጀል የሚቀሰቅስ ወይም የሌሎችን ክብር የሚነካ፣ የሚያዋርድ፣ የሚያንቋሽሽ ለሆነ፡፡

13.8. አብቁተ አ.ማ. የኤም-ብር ተጠቃሚ ሞት ወይም የአዕምሮ ችሎታ ማጣትን እንዲያውቅ በተደረገ ጊዜ የውርስ ወይም የጤና ህግ(እንደ አስፈላጊነቱ) ተፈፃሚ እስኪሆን ድረስ የአካውንቱን እንቅስቃሴ ያግዳል፡፡

13.9. ከላይ ያለው እንዳለ ሆኖ አብቁተ አ.ማ.በሞት ወቅት ወይም የአዕምሮ ችሎታ ሲታጣ ያሉት ኢ-ገንዘብ እንዴት ሆኖ የቅርብ ዘመድ ሊሾም የሚችልበትን መንገድ ያቀርባል፡፡

13.10. የሟችን ወይም የአዕምሮ ችሎታን ያጣን የኤም-ብር ተጠቃሚ ገንዘብ ለመውሰድ አስተዳዳሪ ወይም ውርስ አጣሪ ነኝ ያለ ሰው በአብቁተ አ.ማ. ጠያቂነት አስተዳደርነቱን የሚገልፅ ደብዳቤ፣ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ወይም በአብቁተ አ.ማ. የሚጠየቀውን ሌላ ቅፅ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

13.11. የቅርብ ዘመድ ከሾሙ ወይም ፍርድ ቤት አስተዳዳሪ/ አጣሪ ከሾመ፤ አብቁተ አ.ማ.በእርስዎ ሞት ወይም ቋሚ የሆነ ችሎታ ማጣት ወቅት ይሄን ሹመት ተሞርኩዞ ቀሪ ገንዘቦትን ያስተላልፋል፡፡

## የደንበኛ ድጋፍ

14.1.የመጀመሪያው የርስዎ የድጋፍ መስመር በወኪሎችና በአብቁተ አ.ማ. ቅርጫፎች ይከናወናል፡፡ አብዛኛዎቹ የእርስዎ ጥያቄዎች ወደ ወኪል/ ቅርንጫፍ ይመራሉ፡፡ ወኪል/ቅርጫፍ ለጥያቄዎ አጥጋቢ ምላሽ ለመስጠት ካልቻሉ፤ ለጥያቄዎች በቂ ምላሽ ወዳለው የኤም-ብር የደንበኞች ድጋፍ ማዕከል (ደድማ) ጋር ወኪል/ቅርጫፉ ያገናኝዎታል፡፡ እንደ የንግድ ወይም የኮርፖሬት ደንበኛ በቀጥታ ወደ ደንበኞች ድጋፍ ማዕከል መደወል ይችላሉ፡፡

## ቅሬታ፣ ግጭት መፍቻና ተፈፃሚ ህግ

15.1. አብቁተ አ.ማ.የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ዘርግቷል። የመጀመሪያው ደረጃ ቅርብ ወደሆነው ወኪል/ቅርጫፍ በመሄድ ቅሬታዎን በመግለፅ ማስመዝገብ ይኖርብዎታል። በዚህ ሂደት ውስጥ ወኪል/ቅርጫፉ እገዛ ያደርግሎታል።

15.2. በአንድ አንድ ሁኔታዎች ወስጥ አብቁተ አ.ማ.ከተሳታፊ ነጋዴዎች ጋር በመተባበር የግጭት መፍቻ መንገዶችን ሊያዘጋጅ ይችላል። በነዚህ መፍቻ መንገዶች አብቁተ አ.ማ.ወይም የተሳታፊ ነጋዴዎች/ ንግድ ድርጅቶች ከግዜ ወደ ጊዜ ሃሳብ በሚሰጠው መሰረት ተገገር ይሆናሉ።

15.3. ከዚህ ስምምነት ጋር የተያያዘ ግጭት በወኪል/ቅርንጫፍ ካልተፈታ ወደአብቁተ አ.ማ.ለኤም-ብር አገልግሎት ስራ ኃላፊ ለሆነው ስራ አስኪያጅ መቅረብ አለበት።

15.4. ከዚህ ስምምነት ጋር የተያያዘ ግጭት ለኤም-ብር አገልግሎት ስራ ኃላፊ በሆነው አብቁተ አ.ማ. ስራ አስኪያጅ ካልተፈታ ወደ ግልግል ዳኝነት ይመራል። ይህም በተዋዋዮቹ በተመረጠ አንድ ገላጋይ ይሆናል። ይህ አይነት ስምምነት ከሌለ ደግሞ የግጭቱ መፈጠር ከታወቀ በ60 ቀናት ውስጥ ከተዋዋዮቹ አንዱ አመልክቶ በኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት ተቋም ሊቀመንበር ይከናወናል።

15.5. ህግ እስከፈቀደ ድርስ የግልግል ውሳኔው በቂ፣ የመጨረሻ እና ተዋዋዮቹን የሚገዛ ይሆናል።

15.6. በዚህ ክፍል ያለው በህግ የታወቀን ግጭት ፈቺን ተቋም ይህን ግጭት ለመቀበል፣ ለመስማት ሆነ ለመወሰን እንደሚከለክል ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

15.7. ይህ ውል የሚገዛው እና የሚተረጎመው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐፐሊክ ህግጋት አግባብ መሰረት ነው።